# ዛሬም ወደ ውስጥ የመመልከትን “ግርዶሽ” ገፈን ካልተባበርን-- በተናጠል የትም አንደርስም

(ግርማ በቀለ )

ከዚህ በፊት የመድረክንና የሰማያዊን ጉባኤዎች በሚመለከት የተሰማኝን ትዝብትና ሥጋት በገለጽኩበት ጽሁፌ ያነሳኋቸውን አንዳንድ ጉዳዮች ዛሬም ደግሜ ለማንሳት ግድ ብሎኛል፡፡ በእኔ አተያይ ትዝብቴም ስጋቴም በቦታቸው ናቸውና ‹‹ጩሄቴ›› መቀጠል አለበት፡፡ ጽሁፉን ስጀምር እንዲህ በሚል ነበር፤ ‹‹ የዛሬውን ጽሁፍ በጥያቄ መጀመር ፈለግሁ፡፡ ‹‹ ለሰው ልጅ ከትናንቱ/ከስህተቱ ለመማር ስንት ጊዜ ይፈጅበታል፣ ለመማር ስንቴ መውደቅ ይኖርበታል?›› በሚል፡፡ ይህን ጥያቄ በአገርኛ አባባል በቀላሉ መልሼ ወደ መነሻ ኃሳቤ ላምራ፡፡ ደጋግመን ወድቀናልና መልሱ ‹‹ ጠዋት ስትወጣ የመታህ እንቅፋት/ድንጋይ ማታ ስትመለስ ከደገመህ ድንጋዩ አንተ ነህ፡፡›› የሚለው ይሆናል፡፡›› ዛሬ ላይ ሆኜ ስመለከት ይህ ጥያቄ መልስ እያገኘ ያለ እየሆነብኝ ነው፡፡ የሰበብ ማሳረፊያቿን ‹እንቅፋት›-ህወኃት/ኢህአዴግ ሲፈጠር ጀምሮ ‹‹ድንጋይ›› ስለመሆኑ መስማማት ባለበት በተናጠል እየሄድን የምንገጩውና የምንጋጨው ‹‹እኛ›› ወደ ‹‹ ድንጋይ ›› አልተለወጥንም ብለን ብንከራከር የት ድረስ ያስኬዳል? አሁንም ለመልሱ ወደ ውስጣችን መመልከት ካልቻልን እንቅፋቱ/ድንጋዩ በቦታው ሆኖ እየጠበቀን ነውና አናመልጠውም፡፡ ምን ለማለት ፈልጌ እንደሆነ ጥቂት ላብራራው፡፡

ለዚህ መነሻ እንዲሆነኝ ደግሞ እንደ-ማጠቃለያ ብዬ በመጨረሻ ላይ ያነሳሁትን ልጥቀስ- ‹‹ዛሬ እውነት እውነቱን መነጋገር ከምንገደድበት ደረጃ ደርሰናል፡፡ እስከዛሬ ‹‹ትግሉን ይጎዳል›› እያልን ሃቁን መደበቃችን ማብቃት አለበት እላለሁ፡፡…… በዚህ ወቅት ይህን እንድንል ያስገደደን ደግሞ ስህተቶች ሲደጋገሙና ለውድቀት ሲዳርጉን ማየታችን ብቻም ሳይሆን ካለፈው ‹‹ተማርን›› ብለን ከተማማልን በኋላም ‹‹ድመት መንኩሳ ዐመሏን አትረሳ›› እንዲሉ ሆኖብን ተመሳሳይ ስህተቶች እየፈጸምን በተለመደው የክሽፈት መንገድ ለመቀጠል እየተንደረደርን መሆኑን በማስተዋላችን ማንንም ከማንም ሳንለይ ይብቃንና የጋራ አገር አድን መፍትሄ ለመፈለግ እንነሳ የሚል ጥሪ ለማስተላለፍ ነው፡፡ ›› ይላል፡፡ የዚህ ጥሪ መሰረት ደግሞ በ14ቱ ፓርቲዎች ጥናት ላይ የተገለጸው ‹‹ ኢህአዴግን ጨምሮ-ላለንበት ተጨባጭ ሁኔታ የሚመጥን ዘላቂ መፍትሄ የሚሰጥና የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት የሚችል አንድም ፓርቲ የለም፣….›› የሚለው ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የጥናቱ ባለቤቶች ምን አድርገዋል፣ በሂደቱ የት ደርሰዋል፣ ዛሬስ ምን እየተደረገና እየሆነ ነው፡፡…? አብረን እንመልከት፡፡

ለዚህ አጭር ማሳያ እንዲሆነን የሩቁን ትተን ( ከኢሰዴአኃኅ /1986እስከ ኢተፖዲኅ/1990 ያሉትን ትተን (አብዛኛው የኢተፖዲኅ መስራቾች የኢሰዴአኃ አባላት መሆናቸውን ልብ ይሏል) ከምርጫ 97 ወዲህ ባለው ጊዜ ዲሞክራቲክ የፖለቲካ ፓርቲዎችና አመራሮቻቸው ያሉትን፣ በተደጋጋሚ ምለው የተገዘቱበትን ቃልና ተግባር ጊዜውንና ውጤቱን በትክክል የሚያሳዩ ዋና ዋና የሚባሉ አብነቶችን በመረጃ አስደግፈን እንመልከት፡፡

ታሪካዊውና አይረሴው ምርጫ 97 -- ቅንጅትና ኢዴኃህ፤

በጋራ የወሰዱት አቋም የሰጡት መግለጫ የት ደርሶ ስለምን አንዱ ወደ ቃሊቲ ሌላው ወደ ምክር ቤት ያመሩት?( ሣተናው መስከረም 22፣ሀዳር መስከረም 26/98)፣ አልፎም የቅንጅት አመራር በሁለት ለምን ተከፋፈለ? ይህን በሚመለከት አቶ ልደቱ በራሱ ቃላት….‹‹ ሰፊና ዲሞክራሲዊ ውይይት ተደርጎ… የተሸነፈው/የከሰረው በእርሱ ላይ ብቻ ተንጠልጥሎ የቀረው ‹‹የብቻው የልዩነት ኃሳብ›› ተቀባይነት

ባለማግኘቱ ብቻ፣ … ‹‹ የኢትዮጵያ ህዝብ ከቅንጅቱ ጎን ቆሞ ከመታገል ሌላ አማራጭ አለው ብዬ አላምንም፤እኔም ቢሆን የተሸነፈ ሃሳቤን ይዤ ከቅንጅቱ ጋር ከመቀጠል ሌላ አማራጭ አለ ብዬ አላምንም፡፡›› ስለውህደትም ‹‹…. በተለይ በኢዴአፓ-መድህን በኩል በእርግጠኛነት መናገር የምችለው ከሰባት ቀናት በፊት ምክር ቤታችን ተሰብስቦ የቅንጅቱ የውህደት እንቅስቃሴ በጣም ተጠናክሮ ተግባራዊ መሆን እንዳለበት ወስኗል፡፡… ስለዚህ እኔ ያለሁበት ፓርቲ የቅንጅቱን ወደ ውህደት መሄድ በጣም ነው የሚደግፈው….››እንዲሁም‹‹ …ኢህአዴግ እንደሚያሟርተው ቅንጅቱ እንዲህ በቀላሉ ሊከፋፈል የሚችል አይደለም…›› (ዳግም ወንጭፍ ሰኔ 28/97) እንዳለው ቅንጅትም ችግሩን ለምን ሲሸፋፍን  ቆዬ?ይህን በመጨረሻ ቅንጅት ከደረሰበት ከመፈረካከስ እስከ መካሰስ ውጤት ጋር እናመዛዝነው፡፡

የኢዴፓን አመራር ‹‹ ውሳኔውንም (የምርጫ ቦርድን) አንቀበልም፣ ወደ ፍርድ ቤትም አንሄድም ›› የሚል አቋም ወስዶ ሲያበቃ ( ጦማር ነሃሴ 18/97)  ከተሰጠው ማንዴት ውጪ፣ በድርጅቱ እንዲሁም በዕጩዎችና ተመራጮች  ከተላለፈው ውሳኔ (ብሄራዊ ሎተሪ አዳራሽ) በተቃራኒ  ተጓዘ፣ ስለምን ምክር ቤት ገባ ? ለምን አመራሩ የውጪና አገር ቤት በሚል ተከፋፈለ? ከኢዴፓን የወቅቱ ከመካሰስ እስከወዲያኛው መለያየት  ውጤት አንጻር እንፈትሸው፡፡

ምርጫ 2002-- መድረክና አባላቱ፣

መድረክ-- ከምርጫ 97 የተሻለ ሁኔታ ስለነበር ወይስ …. ሽርፍራፊ የምክር ቤት ወንበር ከተገኘ በሚል ታሳቢ- ወደ ምርጫ የገባው?  በምርጫው ወቅት በመድረክ አባላት መካከል የነበረው ሽኩቻስ ከምን የመነጨ ነበር?  አገሪቱን በየ ‹‹ክልላቸው/ብሄራቸው›› አልተከፋፈሉም ነበርን ወይም ‹‹በድንበር ይገባኛል›› የተነሳው ውዝግብ ከምን የመነጨ ነበር ? ‹‹ብቸኛው›› ተመራጭ ምክር ቤት በመግባቱ ስምምነት ነበርን? በመፈቃቀድና በመተማመን ወይስ በጥርጣሬና መሸካከም እስከተከፋፈሉበት ጊዜ አብረው የተጓዙት? ጊዜ እንጂ እነርሱ አልነገሩንምና…..

ምርጫ 2005— ‹‹33ቱ››

በምርጫ 2005 እንዲስተካከሉ ያቀረቧቸው ጥያቄዎች መልስ ስላገኙ ነው ወደየቤታቸው/ የቀንድ አውጣ ጎጆአቸው/ የገቡት? ወይስ የ2005ቱ ከመንግስት የሚሰጥ የፋይናንስ ድጋፍ ስለሌለው ነበር ላለመግባት የተደረሰው ስምምነት ተግባራዊ የሆነው? ሰማያዊም ስምምነት ፈርሞ ፊርማው ሳይደርቅ ‹‹እነማን ጋር ልተባበር ››ማለቱን እነማን ጋር ለመስራት ተስማማቼ ነበር የሚለውን በግልጽ መልሶት ነበር ወደ ቀጣዩ የ9ኙ ትብብር የመጣውና የማዕከልነት ኃላፊነት የተረከበው?

ምርጫ 2007---

መድረክ እና አንድነት በ14ቱ ፓርቲዎች ጥናት ተካፋይ ሆነው ሳለ ላለመሳተፍ ያቀረቡት ምክንያት በእርግጥ ውኃ የሚያነሳ ነበርን? በምክንያትነት ያቀረቡት ችግር ከተፈታስ በኋላ ለምን ተደጋጋሚ ጥሪ ቀርቦላቸው ከ9ኙ ፓርቲዎች ትብብር አልተቀላቀሉም? እንዲያው የተስማሙት ‹‹የ9ኙ ፓርቲ ትብብር›› አባላት ሳይመካከሩ በተናጠል ወደ ምርጫ ለምን ገቡ? 14ቱ ጥናቱን ሳያነቡ ነው ያጸደቁት  ፣9ኙስ የስምምነት ሰነዱን ሳይመረምሩ ነው የተፈራረሙት ? ‹‹ የነጻነት ለፍትሃዊ ምርጫ›› አጀንዳና ተከትሎ የነበረው ፉከራና ቀረርቶ ለፕሮፖጋንዳ ፍጆታ ነበርን ? ኃሳቡን ያመነጨው ፓርቲ ከሁሉ ቀድሞ ‹‹የምርጫ ግብረ ኃይል ›› ማዋቀሩን ማወጅ ማለት ምን ይሉታል ? ወደምርጫ ከገቡም በኋላ በወላይታ ዞን ችግር ገጠመን ብለው በጋራ ጥያቄ ያቀረቡ 8ቱ ፓርቲዎችስ ጥያቄአቸው ተመልሶ ነው በምርጫው የቀጠሉት ወይስ  ፍርፋሪ ቢገኝ በሚል የተሳሳተ ታሳቢ?

በአንድነትና መኢአድ ውህደት ያለመሳካት/መፍረስ ሆነ ፣ ለሁለቱም ፓርቲዎች ለ‹‹ህገ ወጦች›› መሰጠት እውነት የምርጫ ቦርድና ህወኃት/ኢህአዴግ ሴራ ብቻ ወይስ በውስጥ ችግር  መግቢያ ቀዳዳ አመራርና

አባላት በማመቻቸታቸው ታግዟል? አላመቻቸንም የሚሉ ካሉ ዝርዝር ሂደቱን መረጃ አስደግፎ በማቅረብ መከራከር ይቻላል፡፡ ለውህደቱ መክሸፍም ሆነ ለፓርቲዎቹ ‹‹መሰጠት›› የግለሰቦች ግልጽና ድብቅ እጅ ከውጪና ከአገር ቤት አልነበረም ? በምርጫ 2005 እንዲስተካከሉ ያቀረቧቸው ጥያቄዎች ባልተመለሱበት በአንድነት ‹‹ያለ ቅድመ ሁኔታ ›› በምርጫ ለመሳተፍ ለምንና እንዴት  ተወሰነ- በምርጫው አሸንፎ ለመውጣት ወይስ ከምርጫ ቦርድ የኩዴታውን አመራር ዕውቅና ለማግኘት እጅ መንሻነት? እነዚህን የወሰነው የአንድነት አመራር ዛሬ ላይ ከፓርቲ ፖለቲካ ነጻ ነውና ለቀጣዩ ትግል አቅጣጫ ለማመላከት እንዲረዳ  ግልጽ መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡  ሆኖም ዛሬም ‹‹መፍረስን›› ‹‹ድል እና ጀግንነት›› ለማድረግና በሌላው ላይ ጣት ለመጠንቆል ሲታትሩ ስመለከት ዛሬም ከበሽታው አልተፈወሱምና የማቀርበው ጥሪ ‹‹የየዋህ›› ሆኖ ይሰማኛል፡፡ ግን ተስፋ አልቆርጥምና…እጮኃለሁ//

ከምርጫው በኋላስ ቢሆን መድረክና ሰማያዊ ለምን ተመሳሳይ አቋማቸውን በጋራ መግለጽ አልቻሉም? ለዚህ ስለጉባኤዎቹ የጻፍኩትን ትዝብትና ስጋት ይመልከቱ//

ዛሬ በነዚህና በተመሳሳይ ችግሮች የተፈጠሩ ምርጫ ቦርድ በዝርዝሩ 75 ፓርቲዎች ያሳየናል፡፡ አዎን ከ70 የፖለቲካ ፓርቲዎች 58ቱ በምርጫ ተሳተፉ ሲባልና ለህወኃት/ኢህአዴግ ፕሮፖጋንዳ ሲውል ሰምተናል-- ግን ከ1983 እስከዛሬ ያሉ ፓርቲዎቸና አመራራቸው በ3 ቦታ እየተቆጠሩ ለምሳሌ /ሀብዴድ፣ ኢሶማዴ-ደቡብ ኅብረትና መድረክ ወይም ጋዴህ፣ ደኢህዴአግ፣ ኢፍዴአግ/ በየአምስት ዓመት ከመንግስት የምትጣለውን የምርጫ ፍርፋሪ ይጠባበቃሉ፡፡ እንዲሁ እያለ መድረክ ለምን እንደማይዋሃድ ሳይነግረን ለዓመታት በግንባርነት ዘለቀ፤  በ33ቱም በ14ቱም….ተሳተፈ ግን አፍሮ ሩጫውን አቋርጦ ወጣ፡፡ በዚህ መሰረት  አንድ የፓርቲ አባል ሶስት ጊዜ እየተቆጠረ ነው፡፡በተጨማሪም በህይወት የሌሉ ፓርቲዎች እየተጠቀሱ /አንዳንዶችም ለትግል የተሰጣቸውን ቢሮ እያከራዩ/ ያሉ (ጣህዴኅ፣የብዲን፣ ጋኅህዴአ፣ኢብአፓ፣ መኢዴፓ…) ተቆጥረው 70 /75 ፓርቲዎች መባሉን  ስንቱ ያውቅ ይሆን…?  በዚህና በ‹‹አንዱ ቢወድቅብኝ ባንዱ እንጠለጠላለሁ››….. ስሜት ጉዞው  ቀጥሏል፤ ግን የተለየ ነገር ይዞ አይደለምና ምንም ውጤት አያመጣም፣ ህዝብን አላስፈላጊ ዋጋ ማስከፈሉ ግን አይቀርም፡፡ እዚህ ላይ እነርሱ  ብቻ ሳይሆን አብረው እየወደቁ እየተነሱ ያሉትም  ይህን ጥያቄ ባለማንሳታቸው ከተደጋጋሚ ክሽፈቱ የድርሻቸውን ያነሳሉ፤ ከተግባር አንጻር በትክክልና በግልጽ ቢቆጠር ሃቀኛ (የህወኃት ስሪቶችን ትተን) የለውጥ ኃይሉ ቁጥር ደርዘን  አይሞላም፤ ግልጽ የዓላማና ርዕዮት ልዩነት አለን ቢሉም ቢበዛ በሁለት የሚጠቃለሉ ናቸው፡፡ እዚህ ላይ በአገሪቱ ያሉት የአብዛኛው የለውጥ ኃይሎች መሰረታቸው ከመዐህድና አማራዊ ኃይሎች ውጪ ያለመሆኑንና አንድ ታጋይ በ3 እና 4 ፓርቲ ውስጥ ያለፈ መሆኑን ስንቱ ያውቅ ይሆን? እዚህ ላይ የተነሱትን አሌ የሚል ካለ  በመረጃና ማስረጃ እንነጋገር፡፡

እንዲያው ለሁሉም ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጥቅል የአመራርና አደረጃጀት ጥያቄዎች ከሚያነሱት አጀንዳ፣ ከሚገቡልን ቃል ፣ ከሚነግሩን ዕቅድና ግብ…. አንጻር  አንስተን  ስንቶቻችን  የጋራም ሆነ የተናጠል እንቅስቃሴአችንን ለቀጣይ ትግላችን ግብአት በሚሆን ዓላማ በግልጽ ተወያይተንበት እናውቃለን ?፣ ሌላው ቀርቶ በማዕከላዊ ም/ቤት … ስብሰባዎቻችን የሚነሱ የኃሳብ ልዩነቶችን፣ እንደ ድክመት የነሱ ጉዳዮችን ለቀጣይ ትግል በገንቢነታቸው እንጠቀማለን ወይስ በተቃራኒው በነዚህ ምክንያት አልተፈራረጅንም ፣ በመካከላችን ያለው መተማመንና አብሮነት ለችግር አልተዳረገም (ለህወኃት ውስጣችን እንዲገባ ቀዳዳ አላበጀንም) ?፣ በመቻቻል ስም አልተሸካከምንም/ አልተሸፋፈንም/እየተሸፋፈንንና እየሸፋፈንን አይደለም ? ….. እነዚህና የመሳሰሉ ድክመቶቻችንን በመማሪያነት ተጠቅመን ለቀጣዩ ትግል ትምህርት ለመውሰድ፣ ከተለመደው አስተሳሰብ ለመላቀቅ ዛሬስ (ፓርቲያችንን ‹‹ተነጠቅን/ተቀማን›› የሚሉትን ጨምሮ) የተዘጋጀን ስንቶቻችን ነን? ዛሬስ ፓርቲዎች ‹‹ከፈረሱ/ከተነጠቁ›› በኋላ  እንኳ በትናንቱ ‹‹ እንደ ጀብድ›› በሚነገረው ኃሳብና ድርጊት ዙሪያ በአንድነት የቆማችሁ ናችሁ ወይስ በሶስትና አራት ቦታ ተከፋፍላችሁ ማዶ ለማዶ እየተያያችሁ ወይም እየተናቆራችሁ ነው ያላችሁት… ለምን? እነዚህን በግልጽ ለመወያየት ድፍረቱና ዝግጅቱ አለን ?  ሲጠቃለል፣ ማንንም ከማን ሳንለይ ሁላችንም ይህ ዝግጅት በሌለን ሁኔታ በቀጣይም ለዚህ ባልተዘጋጀንበት  ውጤታማ መሆን ይቻላል?  በእኔ በኩል

የጥያቄዎቹ መልሶች ላለፈውም ሆነ ለቀጣዩ ‹‹ አሉታዊ›› ነውና ለቀጣይ ለመማር፣ ለመስተካከልና ለማስተካከል በግልና በድርጅት ወደ ውስጥ ለመመልከት ራሳችንን እስካላዘጋጀን የትም አንደርስም ፡፡ አራት ነጥብ ልበል ወይስ …. ፡፡ እስኪ ከላይ ያነሳሁትን በበቂ ይቅርና በሚቻለው መጠን አድርጌኣለሁ ፣ግዳጄን ተወጥቻለሁ የሚል  ግለሰብም ሆነ እንደ ስብስብ  እንደ እኔ ‹‹ በስሙ ››ይቅረብና በመረጃ፣ ማስረጃና ሎጂክ ተደግፈን በግልጽ እንከራከር፤ግብዣዬ ነው ፡፡

ከላይ ለአብነት  ያነሳኋቸው ጉዳዮች ከቃልና ተግባር አንጻር ተመልከቱልኝ ፡፡ በእኔ በኩል ሁለት ነገሮችን ለማሳየት ነው፡፡ አንድም ድርጅቶች/ፓርቲዎች በሚወስዱት አቋም ላይ ያላቸውን የጽናት ጉድለትና አጀንዳቸውን በየቦታው እያንጠባጠቡ….. ስምምነታቸውን እየጣሱ በበነጋው ተነስተው ሌላ ቅንጅት፣ ግንባር፣ ትብብር …መሰረትን እያሉ በህዝብ ስም እየቀለዱ መሆኑን፤ ሌላውም ፓርቲዎችም ሆነ አመራራቸው ይህን አድርገን ተነስተን ማንም ጠያቂ ስለሌለብን ‹‹ጥናት አድረገን፣ ችግራችንን አበጥረን፣ መፍትሄ አበጅተን… በአደባባይ ተናግረን ብስራቱ በበቂ ሳይሰራጭና ሳይዳረስ፣ፊርማችን ሳይደርቅ … ዛሬም በተመሳሳይ መንገድ በመጓዝ  ላይ መሆናችንን ነው፡፡ በመሆኑም አመንን አላመንን፣ ወደድንም ጠላን… በፖለቲካው ህወኃት (ኢህአዴግ ጭምብል ወሳኙ ህወኃት ነው ማለቴ ይታወስ) በሰፊ ነጥብ ልዩነት እየመራን ነው፤በራሳችን ድክመት በእጅጉ ተበልጠናል፡፡

ስለሆነም እንዲህ በማለት ኃሳባችን እንቋጫለን ፣ መልዕክታችን እናስተላልፋለን፡፡ እዚህ ላይ የማነሳቸው ኃሳቦች አዲስ አይደሉም ከትናንት ( ከ- ጦቢያ፣ ልሳነ ህዝብ፣ ጦማር፣ ምኒልክ፣ ኢትኦጵ፣ እስከ ፋክት፣….፣ ) እስከ ቅርብ እንደ ፕሬስ ሲያራምዱት የነበረ፣ ዛሬም ግለሰቦች በስቃይ ወህኒ ያሉትን ጨምሮ ከአገር ቤት እንዲሁም ከውጪ  በተደጋጋሚ ሲመክሩንና እየመከሩ ያለ ሃሳብ ቢሆንም ዛሬም ዘላቂ መፍትሄ አልተበጀለትምና ነው፡፡ እንደ መቋጫ---

ዛሬም ታዛቢ፣ ጠያቂ የለም፤ ህዝብ እንደትናንቱ ‹‹የተቃውሞ ጎራውን›› በሰሞናዊ ሆይ-ሆይታ ይደግፋል፣ እስከ መጪው ምርጫ የደረሰበትን ሞትና ስቃይ ይረሳልና 5 ዓመት ተኝተን በምርጫ ሰሞን ብቅ ስንል እንደተለመደው ለቀጣዩ ምርጫ አጃቢያችን ይሆናል፤ በቤታችን ያለውን ህመም ደብቀን /ክደን መቀጠል ይቻለናል…. በሚል ታሳቢ ከሆነ አያስኬድም፡፡ ህዝብ ውጤት የማያመጣ አላስፈላጊ መስዋዕትነት የሚከፈልበት ‹‹ምርጫ›› ላይ ተስፋ ቆርጧል፤ህዝብ ቀርቶ ከፓርቲ ቢሮ የወጡትን  የፖለቲካ አመራሮች ‹‹ሞት/ስቃይ ካልቀረ የተለመደው የጦር ሜዳ የጀግና ሞት/ስቃይ ይሻላል›› የሚለውን መምረጣቸውን-- እነ ብርሃኑን ከወህኒ፣ እነ ተስፋሁንን ከግንባር  ለማስረጃ መጥቀስ በቂ ነውና ልብ ያለው ልብ ይበል፡፡….. ጊዜው ለገዢው ፓርቲ ብቻ ሳይሆን ለተቃዋሚውም ራሱን እንዲለውጥ ከሚያስገድድበት 11ኛው የለውጥ ሰዓት ደርሷል፤ ደወሉ ተደውሏል፤ …….ያለተጠያቂነት ሲጓዙ በተደጋጋሚ የከሸፉና ዛሬም በዚያው መንገድ ለሚጓዙና ለመጓዝ ለሚያስቡ፣ በህዝብ መስዋዕትነት የራሳቸውን ስምና ዝና ለመገንባት ለሚታትሩ ‹‹አይነኬ አመራሮች ›› ጀንበር ጠልቃለች፤ ተቃዋሚን መተቸት፣ መንቀፍ ‹‹ዋናውን ዓላማ›› መጉዳት ነው የሚለውም ሆነ የሚቃወሙትና የሚተቹት ላይ ታርጋ በመለጠፍ ህዝብን ማሳሳት ረፍዶበታል ሳይሆን መሽቶበታል፤ ጨዋታው በመረጃና ማስረጃ እየተደገፉ ህዝብን ከአላስፈላጊ መስዋዕትነት መታደግ ደረጃ ላይ ስለደረሰ ለውጥ የማያመጣና ተቃዋሚዎችን በተስማሙበት በአንድ የማያቆም የምንሳሳለትና ዋጋ የምንከፍልለት  ‹‹ ዋና ዓላማ›› ብሎ ነገር  የለም// ከዚህ አልፎ በታሪክና በትውልድ  ተጠያቂነት ማምለጥ አይቻልም፡፡ የውስጡን ለማያውቀው ህዝብ  ‹‹ጅብ በማያውቁት አገር ሄዶ….›› እንዲሉ  ሆኖብን በምናደርገው ከሌላው የምንጠይቀውን የጎሊና ዳኝነት አቆይተን ማለት ነው፡፡

በተቃዋሚዎች አብሮነት ፣የጠራ ኃሳብ፣ የአቋም ጽናት፣ የአመራር ሥርኣት…ወዘተ ደግመን ደጋግመን የምንጽፈው/የምንጮሄው ማርቲን ሉተር ኪንግ ‹‹ስለሚመለከተን ጉዳይ መናገር ያቆምን እለት ህይወታችን ፍፃሜውን ይጀምራል፡፡›› ካለው ባለፈ ለራሳችን ፍጻሜ መቃብር ከመቆፈር አልፈን ወደ ውጤት ጋት በማያስጠጋ የተናጠል ሩጫ/ ጀብደኝነት ህዝብ እያስጨረስን ከመርዶ ነጋሪ ያለፈ መከታ ባለመስጠታችን ይህንኑ በቀጣይ እንዳይደገም  ለመከላከል  ማለትም ትግሉ ወደ ውጤት እንዲሸጋገር ወይም ህዝብን በከንቱ

**ዋጋ እንዳያስከፍል በሚል ነው፡፡በቀጣይ የለውጥ ትግል ለውጥ እንደሚመጣ ተስፋ በማድረግ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ዊንሰቴን ቸርቺል** ‹‹ You will never reach your destination if you stop and throw stones at every dog that barks.››**እንዳለው ለእያንዳንዱ በሶሻል ሚዲያ ለማነባቸው የተለያዩ ራስን የመከላከል ሲያልፍም የማሳበጥ ግልብ ኃሳቦች ዙሪያ** ‹‹ **ራስን ነጻ የማውጣት-- ወደ ውስጥና ኋላ/ያለፈውን ለመመልከት ባለመፍቀድ ለሚቧችረውና ከስህተት ለመማርና ለማስተማር በሩን ለዘጋው** ›› **ሁሉ በየግሉ መልስ ከመስጠት ጠቅለል ባለ መልኩ /ማንንም ከማን ሳንለይ/ ምላሽ ቢሆን በሚል ነው፡፡ እንደ አገር ከገባንበት አዘቅት የምንወጣበትን እና እንደ የለውጥ ኃይል** ‹‹**ከተደጋጋሚ ክሽፈት**›› **የምንመለስበትን ትምህርትና ቅን ልቡና አንድዬ እንዲቸረን፣ በቸር እንዲያገናኘን እየተመኘሁ፣ለዛሬው በዚሁ አበቃሁ፡፡**

ኢትዮሚድያ - Ethiomedia.com
August 31, 2015